የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

ኅዳር 22/2005

# ዓለም አቀፍ የኤይድስ ቀን

በመላው ዓለም ዛሬ ኅዳር 22 የሚከበረው የኤይድስ ቀን ይህ ቀሳፊ በሽታ በሀገራችን ላይ ያደረሰውን ከፍተኛ ጉዳት እንድንመረምር ያስገድደናል ። ያለው አገዛዝ የበሽታውን መጠን ሊደብቅ ቢጥርም፤ ካለፉት አመታት ሲተያይ የበሽተኛው ቁጥር ቀንሷል ቢባልም ብዙ ሚሊዮን ዜጎችን የሚያስቃይና ብዙ መቶ ሺዎችንም የገደለ መቅሰፍት መሆኑ የሚደበቅ አይደለም ።

የ ኤይድስ ስርጭት ከነበረውና ካለው ሥርዓት ጋር የተገናኘም ነው ። ያለፈው አገዛዝ ኤይድስ ምንድነው ሊል ቢቃጣም አንድ ተከላካይ አቋም አቋቁሞ የመከላከል ጥረት አድርጎ ነበር። ይህን ተቋም ሳይውል ሳያድር ወያኔ አፍርሶታል ። በ ኤይድስ መከላከል ሽፋን አዜብ ጎላና ሚቹ አቡን ተብዬ ብዙ ሚሊዮን ዶላር ዘርፍዋል ። በ 1983 የወያኔ ወታደሮች በኤይድስ በስፋት ሲበክሉ ወያኔ እነዚህን በማከም ፈንታ ወደ ሌሎች ክልሎች መላኩና ጉዳት ለማድረስ መጣሩ የተጋነነ ወሬ ተብሎ የሚታለፍ አይደለም ። ኤይድስን በተመለከተ ሰፊ ቅስቅሳ ተደረገ ቢባልም በመሰረቱ ስርዓቱ በሀገር ደረጃ እያስፋፋ ያለው ጸያፍ ስርዓት ትልቁንም ወጣቱንም በሽታ ኣጋልጦታል ። የከተማው ቀርቶ በየገጠሩ ሚሊዩኖች የ ኤይድስ ሰለባ ሆነዋል ። የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣኖችና ጀኔራሎች የበሽታው ተጠቂዎች ናቸው ። ይህን ግን በይፋ አምነው አዲሱን ትውልድ በመምከር ፈንታ መደበቁን መርጠዋል ። ወያኔ የብልግና ስርዓትን እያስፋፋ ነውና ፤ ለባዕዳን ዝቅጠት ሀገሪቷን ክፍት አርጓልና ይህ የዘመኑ በሽታ ሊገደብ የሚችልበት ሰፊ ሁኔታ የለም ። ስለዚህም ዛሬ የ ኤይድስ በሽተኖች ቁጥር ቀነሰ ቢባልም ያለው በሽተኛ ቁጥር በጣም በጣም ብዙ ነው ።

አገዛዙ ብልሹ ነውና ያለው ሁኔታ ቀቢጸ ተስፋን የሚያስፋፋ ነው ። ብዙዎች መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ ለማድረግ ዝግጁ ኣይደሉም ። ወያኔ ታጋዩን የሀገር ወጣት ክፍል በተለይ ከጥቅም ውጪ ማድረግ ይፈልጋልና አልባሌ ልምዶች ወጣቱን እንዲበክሉ ይፈልጋል፡ ይጥራል ። ይህም ለ ኤይድስ ስርጭት እንዲስራ ያደርገዋል ። ወያኔ በኢትዮጵያ ኤይድስ መሰራጨቱን --ከትግራይ ውጪ -- ይፈልገዋል ። በኤይድስ የተያዙትን የሰራዊቱ ኣባሎችን ለምን ከትግራይ ውጪ ኣሰማራ ታዲያ ? መሰል ብዙ ጥያቄዎች ኣሉ ። ዛሬ በዓለም ኣቀፍ ደረጃ የ ኤይድስ ቀን ሲከበር የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ለዚህ ቀሳፊ በሽታ ዛሬም የተጋለጠ መሆኑን በማሳወቅ ነው ። ሀገራችን ለሀገር በቀልም ለባዕዳንም ባለጌዎች በወያኔ መተቃጧንም ማጋለጥ አለብን

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE